## ከዱር እንስሳት ሀብት ጋር በተያያዘ ሀገራችን የተቀበለቻቸው ዓለም-አቀፍ ስምምነቶች

| ተ.ቁ | የድርጅቱ ስም | አባል የሆነበት ዓ.ም | የመዋጮ መጠን በብር | ድርጅቱ ለአባል ሀገሮች የሚሠጠው ጠቀሜታ | ከድርጅቱ እስከ አሁን የተገኘ ጥቅም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ዓለም-አቀፍ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ህብረት (IUCN)<br><br>International Union for the Conservation of Nature | 1959 | 3591 የስዊዝ ፍራንክ<br><br>(ብር 35,497) | ➢ የተፈጥሮ ሀብትን በዓለም-አቀፍ ደረጃ ለመጠበቅና ዘለቄታዊ ጥቅም እንዲሰጡ ለማስቻል የህብረቱን አባል ሀገራትና ተቋማት በማስተባበር በጋራ መስራት የሚችሉበትን ሁኔታ ፈጥሯል፤<br><br>➢ ዘመናዊና ተመራጭ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስልቶችን (ቴክኖሎጂዎችን)፣ ጠቃሚ ልምዶችንና መረጃዎችን በህብረቱ አባል ሀገራትና ተቋማት መሀል በማስፋፋትና በመለዋወጥ የተፈጥሮ ሀብቶቻቸውን በተሻለ እንዲጠብቁ ያስችላል፤<br><br>➢ መንግስታትና ተቋማት የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅና ዘለቄታዊ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ህጎችና ፖሊሲዎች እንዲኖራቸው የማቴሪያልና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፤<br><br>➢ በህብረቱ አባል ሀገራትና ተቋማት በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚሠሩ ጥናትና ምርምሮችን ይደግፋል፤<br><br>➢ አባል ሀገራት የተፈጥሮ ሀብቶቻቸውን ለመጠበቅ የሚመሰርቷቸው የጥበቃ ቦታዎች ዓለም-ዓቀፍ ደረጃን የጠበቁ እንዲሆኑ ቴክኒካል ድጋፍ ያደርጋል፤ በዚህ መልክ ለሚመሠረቱት የጥበቃ ቦታዎችም ዓለም-አቀፍ እውቅና ይሰጣል፤<br><br>➢ በሀብረቱ እውቅና የተሰጣቸው የጥበቃ ቦታዎችም በዓለም ዙሪያ የመታወቅ እድል ስለሚፈጠርላቸው በዚህም በረካታ ተመራማሪዎች ወደ ሀገራችን እንዲመጡ ይጋባዛል፡ ለዱር እንስሳቱ ጥበቃና ልማት አጋዥ የሆኑ ጠቃሚ ግኝቶች ያበረክታል፤ | ✓ ለዱር እንስሳት ሀብት ጥበቃና ዘለቄታዎ አጠቃቀም አጋዥ የሆኑ የተለያዩ ሳይንሳዊ መረጃዎችንና ጠቃሚ የጥበቃ ስልቶችን ማግኘት ተችሏል፤<br><br>✓ ከህብረቱ አባል ሀገራትና ተቋማት ጋር ጠቃሚ ልምዶችን መለዋወጥ ተችሏል፤<br><br>✓ በሀገራችን የተመሠረቱት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ዓለም-አቀፍ ደረጃን የጠበቁ እንዲሆኑ እገዛ ተደርጎልናል፤<br><br>✓ በሀገራችን የተመሠረቱት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎቻች በዓለም-አቀፍ ደረጃ የመታወቅ እድል ስለተፈጠረላቸው በርካታ ተመራማሪዎች ወደ ሀገራችን ሲመጡ ችለዋል፤ በዚህም ከተገኘው ሳይንሳዊና ማህበራዊ ጥቅም ባሻገር ሀገራችን ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ አግኝታለች፤<br><br>✓ የተፈጥሮ ሀብትን ከሌሎች ሀገራት ጋር በጋራ ለመጠበቅ ሀገራችን ያላትን ቁርጠኛነት ያሳያል፤፤ |

* አንድ የስዊዝ ፍራንክ የምንዛሬ መጠን በኢትዮጲያ ብር 9.8850 ነው።

| ተ.ቁ | የድርጅቱ ስም | አባል የሆነበት ዓ.ም | የመዋጮ መጠን በብር | ድርጅቱ ለአባል ሀገሮች የሚሠጠው ጠቀሜታ | ከድርጅቱ እስከ አሁን የተገኘ ጥቅም |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ህልውናቸው በአስጊ ደረጃ ላይ የሚገኙ የዱር እንስሳት እና እጽዋት ዝርያዎች ዓለም -አቀፍ ንግድ ስምምነት (CITES)<br><br>Convention on Internat -ional Trade in Endangered Species of wild fauna and flora | 1981 | 215 የአሜሪካን ዶላር<br><br>(ብር 2494) | ➢ በአለም-አቀፍ ንግድ ምክንያት ህልውናቸው በአስጊ ደረጃ ላይ የሚገኙ የዱር እንስሳት እና እጽዋት ጨርሰው ከምድረ ገፅ እንዳይጠፉ ለማድረግ መንግስታት ተባብረው በጋራ እንዲሠሩ አስችሏል።<br>➢ በአለም አቀፍ ንግድ ምክንያት ህልውናቸው በአስጊ ደረጃ ላይ የሚገኙ የዱር እንስሳት እና እጽዋት የሚደርስባቸውን ጫና በመቀነስ የእንስሳቱና የእጽዋቱ ህልውና ተጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፉ የማድረግ ስራ ያከናውናል።<br>➢ ዘለቄታዊነትና ህጋዊነት ያለው የዱር እንስሳት አጠቃቀምን ያበረታታል።<br>➢ በዱር እንስሳት ዓለም-አቀፍ ንግድ ላይ ተገቢ የቁጥጥር ስልት በማበጀት በአባል ሀገራት ተግባራዊ እንዲደረግ የሚያስችል አንድ ወጥ አሰራር በመዘርጋት አባል ሀገራት እየተናበቡ እንዲሰሩ አስችሏል።<br>➢ ለስምምነቱ አባል ሀገራት የሚመለከታቸው ባከለሙያዎችና ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ሙያዊ ስልጠናዎች ይሰጣል።<br>➢ አባል ሀገራት ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችላቸው በሚያወጧቸው እቅድ መሠረት የቴክኒክ፣ የማቴሪያልና የገንዘብ አገዛ ያደርጋል።<br>➢ ስምምነቱ በሚያዘጋጃቸው ልዩ ልዩ ዓለም-አቀፍ ስልጠናዎችና ስብሰባዎች ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች የመሳተፍ እድል ይሠጣል። በዚህም ከተለያዩ አባል ሀገራት ጋር የልምድ ልውውጥ ለማድረግና ጠቃሚ ልምዶችን ለመቅሰም ያስችላል። | ✓ ዝሆንን ጨምሮ በዚህ ስምምነት ተመዝግበው በሚገኙ የተለያዩ የሀገራችን የዱር እንስሳት ላይ የሚፈፀመውን ህገ-ወጥ አለም-አቀፍ ንግድ ከአባል ሀገራት ጋር በጋራ የመቆጣጠር ስራ እየተሰራ ይገኛል።<br>✓ በዱር እንስሳቱ ላይ የሚፈፀሙትን ህገ-ወጥ ድንበር ዘለል ንግድ በተሻለ ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የባለሙያዎችን አቅም የሚያጎለብቱ የተለያዩ ስልጠናዎች ተሠጥተዋል<br>✓ በዱር እንስሳቱ ላይ የሚፈፀሙትን ህገ-ወጥ አለምአቀፍ ንግድ በመከላከል ዘለቄታዊነትና ህጋዊነት ያለው አጠቃቀም እንዲሠፍን አስችሏል።<br>✓ ስምምነቱ በሚያዘጋጃቸው ዓለም-አቀፍ ስብሰባዎች በመሳተፍ የልምድ ልውውጥ ማድረግና ጠቃሚ ልምዶችን መቅሰም የተቻለ ከመሆኑም በላይ በሀገራችን ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ለማስተዋወቅ አጋጥሚ ፈጥሮአል። |

* አንድ የአሜሪካን ዶላር የምንዛሬ መጠን በኢትዮጲያ ብር 11.60 ነው፡፡

| ተ.ቁ | የድርጅቱ ስም | አባል የሆነበት ዓ.ም | የመዋጮ መጠን በብር | ድርጅቱ ለአባል ሀገሮች የሚሠጠው ጠቀሜታ | ከድርጅቱ እስከ አሁን የተገኘ ጥቅም |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | ዓለም-አቀፍ የስደተኛ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ስምምነት (CMS)<br><br>Convention on Migratory Species of wild animals | 2001 | 500 ዩሮ<br><br>(ብር 7,000) | ➢ ዘለቄታዊ አጠቃቀምን ጨምሮ ሀገሪቱ ስደተኛ ዝርያዎችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመንከባከብ ቁርጠኝነቷን ታሳያለች፤<br><br>➢ የስደተኛ ዝርያዎች የጥበቃ ሥራ ለቀጣዩ ትውልድ ጥቅም በማረጋገጥ ፋይዳ ያላቸው የተፈጥሮ ሀብቶችን በዘላቂነት ለመጠቀም ሕጋዊና ቴክኒካዊ አቅምን ታጠናክራለች፤<br><br>➢ አንድ ዓይነት ስደተኛ ዝርያዎችን ከሚጋሩ አገሮች ጋር ከሚደረግ ትብብር ወይም ተመሣሣይ የጥበቃ ችግሮች ካሉባቸው ሀገሮች ከሚደረግ ትብብር ጥቅም ታገኛለች፤<br><br>➢ ወቅታዊና ጠቀሜታ ያላቸውን ቴክኖሎጂዎችን እና መረጃዎችን ከማግኘት በተጨማሪ በመረጃ ልውውጥና ከዓለም አቀፍ ባለሙያዎች የምታገኘው ጥቅም ይዳብራል፤<br><br>➢ የመምረጥና የመመረጥ መብትን ጭምር ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውሣኔዎች በሚተላለፉበት ጊዜ ለምሳሌ የገንዘብ አመዳደብን በተመለከተ፣ የየሦስት ዓመቱ የሥራ ፕሮግራሞች በሚዘጋጁበት ጊዜ ፣የፋይናንስ ደንቦችና ህጐች በሚፀድቁበት ጊዜ እንዲሁም በዝርዝር ውሣኔዎችና የመፍትሄ ሀሳቦች ላይ ሀገሪቱ ሀሳቦችን የማንሸራሸር ሙሉ ሥልጣን ይኖራታል፤<br><br>➢ ሀገሪቱ በተለያዩ የኮንቬንሽኑ አካላት ባሉ ሥራዎች ውስጥ የመሣተፍ መብት ይኖራታል፣ ማለትም በሥሩ በሚደራጁ የConvention on Migratory Species ሣይንሳዊ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴና የሥራ ቡድኖች ውስጥ /Working groups/ ለማሳተፍ ያስችላታል፤<br><br>➢ ስምምነቱ በሚያካሄዳቸው ልዩ ልዩ ዓለም-አቀፍ ስልጠናዎችና ስብሰባዎች ለመሳተፍ እድል ይኖራል፤ | ✓ ምንም እንኳ አባል የሆንነው ገና በዚህ ዓመት ቢሆንም ቀደም ሲል ስምምነቱ በሚያዘጋጃቸው ዓለም-አቀፍ ስብሰባዎች በተመልካችነት እየተጋበዝን የተሳተፍን ሲሆን በዚህም የተለያዩ ጠቃሚ ልምዶችን አግኝተናል፤ |

* የአንድ ዩሮ የምንዛሬ መጠን በኢትዮጲያ ብር 14.00 ነው::

| ተ.ቁ | የድርጅቱ ስም | አባል የሆነበት ዓ.ም | የመዋጮ መጠን በብር | ድርጅቱ ለአባል ሀገሮች የሚሠጠው ጠቀሜታ | ከድርጅቱ እስከ አሁን የተገኘ ጥቅም |
|---|---|---|---|---|---|
| 4 | የአፍሪካ፣ አውሮፓና ከፊል እስያ ስደተኛ አእዋፍ ስምምነት (AEWA)<br><br>African - Eurasian migratory Water bird Agreement | 2001 | 500 ዩሮ<br><br>(ብር 7,000) | ➢ ስምምነቱ በአቅም ግንባታ መስኮች የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፤<br><br>➢ በመስኩ ለተሰማሩ ባለሙያዎች ሥልጠና መስጠት፤<br><br>➢ የአካባቢው ሕብረተሰብ ስለ ተሰዳጅ የውሃ አዕዋፋት ያለውን ግንዛቤ በማሳደግ፤<br><br>➢ ባለፉት ዓመታት ለዓለም ከፍተኛ ስጋት ሆኖ የነበረው የአዕዋፋት ኢንፍሉዌንዛን መረጃ በቀላሉ ለማግኘትና አስፈላጊ የሆኑ የጥንቃቄ ዕርምጃዎችን ለመውሰድ ጠቀሜታው የጎላ ነው፤<br><br>➢ ስምምነቱ በሚያካሄዳቸው ልዩ ልዩ ዓለም-አቀፍ ስልጠናዎችና ስብሰባዎች ለመሳተፍ እድል ይኖራል፤ | ✓ ምንም እንኳ አባል የሆንነው ገና በዚህ ዓመት ቢሆንም ቀደም ሲል ስምምነቱ በሚያዘጋጃቸው ዓለም - አቀፍ ስብሰባዎች በተመልካችነት እየተጋበዝን የተሳተፍን ሲሆን በዚህም የተለያዩ ጠቃሚ ልምዶችን አግኝተናል፤<br><br>-- |

* የአንድ ዩሮ የምንዛሬ መጠን በኢትዮጲያ ብር 14.00 ነው።

በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
ለሰው ኃብትና ንብረት ሥራ አመራር መምሪያ
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡ <u>ከዱር እንስሳት ሀብት ጋር በተያያዘ አገራችን የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ይመለከታል፡፡</u>

ከፍ ብሎ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሀገራችን የዱር እንስሳት ሀብቷን በተሻለ ለመጠበቅና ለመጠቀም የሚያግዙ የተለያዩ አለም-አቀፍ ስምምነቶችን ተቀብላ በመስራት ላይ እንደምትገኝ የሚታወቅ ሲሆን የእነዚህኑ ዓለም-አቀፍ ስምምነቶች ስም፣ አባል የሆንበት ዓ.ም፣ ለድርጅቶቹ የሚከፈለው ዓመታዊ የመዋጮ መጠንና ስምምነቶቹ ወይንም ድርጅቶቹ የሚያስገኙትን ጥቅም በተመለከተ መረጃ እንዲሳከላችሁ በቁጥር 5/መ-31/37 መጋቢት 17 2001ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ መጠየቃችሁ ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሠረት ሀገራችን ከዱር እንስሳት ሀብት ጥበቃ አንጻር የተቀበለቻቸውን 4 ዓለም-አቀፍ ስምምነቶች በተመለከተ ዝርዝር መረጃ የያዘ 4 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆናችንን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለዋና ዳይሬክተሩ ጽ/ቤት
- ለዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት
  <u>አዲስ አበባ</u>